# የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር
# የ1996 በጀት ዓመት የመንግሥት አጠቃላይ
# ገቢና ወጪ ሂሣብ ኦዲት ውጤትና አስተያየት

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 68/1989 በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የፌዴራል መንግሥት ያለፈውን በጀት ዓመት ገቢና ወጪ፣ ሀብትና ዕዳ እንዲሁም የመንግሥት ገንዘብ ነክ የሆኑ የሂሣብ መረጃዎችን የበጀቱ ዓመት እንደተጠናቀቀ በተቻለ ፍጥነት ዘግቶ ለኦዲት ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት እንደሚልክና የዋናው ኦዲተር መ/ቤትም የሂሣብ መግለጫው በደረሰው በአራት ወራት ጊዜ ውስጥ ኦዲት አድርጎ ሪፖርቱን ከነአስተያየቱ ለሚኒስቴሩ መላክ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

በዚሁ መሠረት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀረበውን የገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ የኢትዮጵያ የመንግሥት ሂሳብ የኦዲት ደረጃዎችን (Ethiopian Government Audit Standards) ተከትለን ኦዲት አድርገናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት የሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀረባቸው የፌዴራል መንግሥት የ1996 በጀት ዓመት የገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ፣ የሂሣብ መዛግብት ሰነዶችና ሌሎች የሂሣብ መግለጫዎች እንዲሁም በኦዲቱ ወቅት ኦዲት አስደራጊዎች የሰጧቸው ማብራሪያዎች ናቸው፡፡

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሂሣብ መግለጫዎች በተሟላ ሁኔታ መዘጋጀታቸውን፣ ዝርዝር የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች ህጎችን ደንቦችንና መመሪያዎችን በመከተል መፈፀማቸውን የማረጋገጥ እንዲሁም ተገቢውን የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በመዘርጋት አፈፃፀሙን የመከታተል ኃላፊነት አለበት፡፡

በአዋጅ ቁጥር 68/1989 መሠረት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተዘጋጁት የመንግሥት ሂሣብ መግለጫዎች የፋይናንስ አዋጅ ደንብና መመሪያዎችን ተከትለው መዘጋጀታቸውን በኦዲት በማረጋገጥ ነፃ አስተያየት መስጠትና ሪፖርት ማቅረብ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ በናሙና በተመረጡ ሂሣቦች ላይ የተከናወነ ሲሆን የተሟላና ተገቢ ማስረጃ መኖሩን፣ የፋይናንስ ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች ተከብረውና የውስጥ ቁጥጥር

ሥርዓቶች ተጠብቀው ዝርዝር የሒሣብ እንቅስቃሴዎች መፈፀማቸውን እና የሒሣብ መግለጫዎች በተሟላ ሁኔታ መዘጋጀታቸውን ማረጋገጥ ያካተተ ነው::

የቀረበውን የገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ አስተማማኝነት ለማረጋገጥ እንዲያስችለን ጉልህ የሆኑ ስህተቶች አለመፈፀማቸውን ለማረጋገጥ የሚረዳ የተሟላ ማስረጃና ማብራሪያ ለማግኘት በሚያግዝ ደረጃ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

አስተያየታችንን ለመስጠት እንዲያስችለን በሒሣብ መግለጫው የቀረበው የበጀት ዓመቱ የገቢና የወጪ ሒሣብ፣ እንዲሁም የሒሣብ ማስረጃ ጥንቅር አመዘጋገብ ሲታይ፣

1. ለክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች የተላለፈው የድጋፍና ልዩ ድጎማ በጀት ብር 5,312.9 ሚሊዮን የሂሳብ ሪፖርት ሳይቀርብ በቀጥታ ሥራ ላይ እንደዋለ ተደርጎ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል::

   የቀረበውም ዓመታዊ የገቢና ወጪ ሒሣብ ሪፖርት በሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 79 መሠረት የክልል መንግሥታት እና የከተማ መስተዳድሮች የድጋፍ በጀት አፈፃፀም ከፋይናንስ ዕቅዱ ጋር በማነፃፀር የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን የፋይናንስ ሁኔታ በሚያሳይ መልኩ አልተዘጋጀም::

   ይህንን አስመልክቶ የመጨረሻ እልባት ለመስጠት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት እና በዋና ኦዲተር መ/ቤት ከፍተኛ ኃላፊዎች ደረጃ ውይይት ተደርጓል በዚህም መሠረት ለክልሎች የተላለፈው በጀት ሥራ ላይ እንደዋለ ተቆጥሮ በወጪ መመዝገብ እንደሌለበት እና በሒሣብ መግለጫው ውስጥ መካተት ያለበት ሂሳብ ሥራ ላይ የዋለው ትክክለኛው ወጪ መሆን እንደሚገባው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ከፍተኛ ኃላፊዎች ደረጃ ስምምነት ላይ የተደረሰ ሲሆን ከሂሳብ አያያዝ እና ከኦዲት አንፃር በማየት ሂሳቡ በወጪ የሚመዘገብበትን ሁኔታ የሚያጠና ከሁለቱ መ/ቤቶች የተወጣጡ አባላት ያሉበት የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሟል::

2. በአዋጅ ቁጥር 25/84 እንደገና የተቋቋሙ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 163/71 መሠረት የሚፈለግባቸውን ውዝፍ የመንግሥት ዋና ገንዘብ እና የዘቀጠ ትርፍ ክፍያ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 25/84 ያልተቋቋሙት ደግሞ የመንግሥት ገንዘብ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠርና ለማስተባበር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 163/71 ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 121/1987 አስቀድሞ

ያልተከፈለ ውዝፍ የዋና ገንዘብ ክፍያ እና የዘቀጠ ትርፍ እንዲሁም ከማሻሻያ አዋጅ ጀምሮ ማንኛውም የመንግሥት የልማት ድርጅት ወይም የገንዘብ ድርጅት የዘቀጠ ትርፍ በየበጀት ዓመቱ መሰብሰብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ በነዚህ አዋጆች መሠረት ከእያንዳንዱ ድርጅት ሊሰበሰብ የሚገባው ገቢ መሰብሰቡን ለማጣራት ተሞክሮ የውዝፍ ዕዳ መከታተያ መዝገብ ከማስረጃዎች ጋር ለማገናዘብ በሚያስችል መልኩ ማጠቃቀሻ የሌለው በመሆኑ እና ማስረጃዎቹም በተሟላና ለኦዲት አመቺ በሆነ መልኩ ተዘጋጅተው ለኦዲት ባለመቅረባቸው በድርጅቶቹ ስም የተከፈቱ ሌጀሮች በአብዛኛው በእርሳስ የተመዘገቡ ሆነው በመገኘታቸው እና ለኦዲት የሚፈለጉ የድርጅቶች ፋይል በቀላሉና በአጭር ጊዜ ለማግኘት ያልተቻለ በመሆኑ ሊሰበሰብ የሚገባው የመንግሥት ገንዘብ መሰብሰቡን ማጣራት አልተቻለም፡፡

3. መንግሥት ከውጭ አገር ተበድሮ ለልማት ድርጅቶች ካበደረው ሂሳብ ውስጥ ከኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን (8 ብድሮች) እስከ ሰኔ 30/1996 ዓ.ም ድረስ ያልተሰበሰበ ከአንድ አመት እስከ 10 ዓመታት እና ከዚያም በላይ በውዝፍነት የቆየ የዋና ገንዘብ (Principal) ብር 52.57 ሚሊዮን እንዲሁም የብድር ወለድ (Interest) ብር 73.99 ሚሊዮን በድምሩ 126.56 ሚሊዮን ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ ያልተሰበሰበውም ሂሳብ በሂሳብ መግለጫው ውስጥ አልተመለከተም፡፡

4. ብሔራዊ ባንክ በሚልከው የአገር ውስጥ ብድር ማስታወቂያና የሚኒስቴር መ/ቤቱ የብድር አስተዳደር መምሪያ በያዘው የሂሳብ መዝገብ መካከል ሰኔ 30/1996 ከወጪ ቀሪ ሂሳብ ትሬዠሪ ቢል በብር 3,306.9 ሚሊዮን እንዲሁም የቦንድ ቀሪ ዕዳ በብር 238.5 ሚሊዮን የብሔራዊ ባንክ የሂሳብ ማስታወቂያ ላይ የተመለከተው ሂሳብ አንሶ መገኘቱና የልዩነቱም መንስኤ በወቅቱ የሂሳብ ማስታረቂያ በመስራት እንዲስተካከል ሳይደረግ ተገኝቷል፡፡ ለወደፊቱ የሂሳብ ማስታረቅ ሥራ በየጊዜው እንደሚሰራ የሚኒስቴር መ/ቤቱ የብድር አስተዳደር መምሪያ ምላሽ ሰጥቷል፡፡

5. በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ደንብ መሠረት የበጀት ዝውውር ሳይፈጸም ወይም ተጨማሪ በጀት ሳይታወጅ የተለያዩ ባለበጀት መ/ቤቶች በዋና ዋና የሂሳብ መደቦች ብር 163.56 ሚሊዮን ከተደለደለው በጀት በላይ ተጠቅመው ተገኝተዋል፡፡ ከበጀት በላይ የተጠቀሙት መ/ቤቶች የተጠቀሙበትን ምክንያት የሚገልጽ ዘገባ እንዲያቀርቡ በማድረግ ሂሳቡን በወጪ ከመመዝገብ በስተቀር ከበጀት በላይ በተጠቀሙ መ/ቤቶች ላይ ምንም የተወሰደ እርምጃ የለም፡፡ ይሁን እንጂ ለወደፊቱ

ተመሳሳይ ሁኔታዎችን ለማስተካከል የበጀት ዝውውር መመሪያ በመዘጋጀት ላይ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ተጠቅሷል።

6. በገንዘብና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 25(3) መሠረት መንግሥት ከአገር ውስጥ ሊበደር የሚገባው የግምጃ ቤት ሰነድ ባለፉት ተከታታይ በጀት ዓመታት ውስጥ በተሰበሰበው አማካይ የመደበኛ ገቢ ከሀያ አምስት (25%) በመቶ መብለጥ እንደሌለበት የተደነገገ ቢሆንም በበጀት ዓመቱ ውስጥ መንግሥት መበደር ከሚገባው በላይ ብር 1,245.4 ሚሊዮን ከግምጃ ቤት ሰነድ ሽያጭ የተገኘ መሆኑ ተረጋግጧል።

7. የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በቻናል 2 የተገኘን እርዳታ በሂሳብ መግለጫው ውስጥ ለማካተት እያንዳንዱ መ/ቤት ያገኘውን እርዳታ እንዲያሳውቅ ደብዳቤ መፃፍ፣ የተለየ የእርዳታ የባንክ ሂሳብ እንዲከፈት ማድረግ እና መ/ቤቶች በእርዳታ ያገኙትን ገንዘብ ሥራ ላይ አውለው በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት ሪፖርት ሲያቀርቡ ሂሳቡን የመመዝገብ ተግባር እያከናወነ ቢሆንም፣ ባለበጀት መ/ቤቶች በቻናል 2 ያገኙትን እርዳታ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሳያሳውቁ ቢቀሩ ሪፖርት ያላደረጉትን መ/ቤቶች ለማወቅና ክትትል ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ባለመኖሩ በቀረበው የሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የእርዳታ ገቢ ሂሳብ መንግሥት በበጀት ዓመቱ ያገኘው ዕርዳታ ይህ ብቻ ነው ብሎ ለማረጋገጥ አያስችልም። ለወደፊቱ አሰራሩን ለማሻሻል ለሚመለከታቸው የሥራ ክፍሎች መመሪያ መተላለፉን በኦዲቱ ወቅት ለመገንዘብ ችለናል።

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 7 በዝርዝር ከተገለፁት ልዩ ልዩ የአሰራር ግድፈቶች በስተቀር በእኛ አስተያየት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ የቀረበው የመንግሥት አጠቃላይ የገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ የዘመኑን የመንግሥት ሂሣብና የፋይናንስ አፈፃፀም በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያል።

ከዚህ በላይ የተመለከቱት ግኝቶች ዝርዝር ሁኔታዎችና የመፍትሄ ሀሳቦች በሪፖርቱ ከገጽ 5 ጀምሮ ተመልክቷል።

# የፌዴራል ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር

# የ1996 በጀት ዓመት የገቢና የወጪ ሂሣብ

# ኦዲት ግኝትና የማሻሻያ ሃሳቦች

በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በቀረበው ዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሣብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የበጀት ዓመቱ ገቢና ወጪ ሂሣብ በበጀት አዋጁ መሠረት መሰብሰቡንና ወጪ መሆኑን ሂሣቡም በትክክል የተያዘ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

1. በበጀት ስለተያዘውና ስለተሰበሰበው ገቢ

በፌዴራል መንግሥት አጠቃላይ የገቢ እቅድ በ1996 በጀት ዓመት ይሰበሰባል ተብሎ በነጋሪት ጋዜጣ የታወጀውና በተጨማሪ በጀት የተያዘው ብር 21,580.00 ሚሊዮን ሲሆን የተሰበሰበው ብር 18,317.00 ሚሊዮን ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህም ከእቅዱ በብር 3,263.00 ሚሊዮን አንሷል፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| የገቢው ዓይነት | የተስተካከለ በጀት /በሚሊዮን/ | | የተሰበሰበ ገቢ /በሚሊዮን/ | | የተሰበሰበው ገቢ በመብለጥ /በማነስ/ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የታክስ ገቢ | 9572 | - | 8397 | - | (1175) | - |
| ታክስ ያልሆኑ ገቢዎች | 1945 | - | 1806 | - | (139) | - |
| የካፒታል ገቢ | 360 | - | 193 | - | (167) | - |
| የውጭ አገር እርዳታ | 6140 | - | 5691 | - | (449) | - |
| የውጭ አገር ብድር | 3563 | - | 2230 | - | (1333) | - |
| | 21580 | - | 18317 | - | (3263) | - |

ከላይ እንደተመለከተው ብር 3,263.00 ሚሊዮን በእቅዱ መሠረት ሳይሰበሰብ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የበጀት እቅድ በሚዘጋጅበት ወቅት በበቂ ጥናትና መረጃ ላይ የተደገፈ መሆን ስላለበት ለወደፊቱ በበጀት ዝግጅት ላይ ተገቢው ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል፡፡

2. የኢንቨስትመንት ገቢ

በአዋጅ ቁጥር 25/84 እንደገና የተቋቋሙ የመንግሥት ድርጅቶች ቀደም ሲል በአዋጅ ቁጥር 163/71 መሠረት የሚፈለግባቸውን ውዝፍ የመንግሥት ዋና ገንዘብና የዘቀጠ ትርፍ ክፍያ መክፈል ያለባቸው ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 25/84

ደግሞ የትርፍ ድርሻ ለመንግሥት ገቢ እንዲያደርጉ ተደንግጓል፡፡ በዚህ አዋጅ ያልተቋቋሙት ደግሞ የመንግሥት ገንዘብ እንቅስቃሴን ለመቆጣጠርና ለማስተባበር የወጣውን አዋጅ ቁጥር 163/71 ለማሻሻል ከወጣው አዋጅ ቁጥር 121/87 አስቀድሞ ያልተከፈለ ውዝፍ የዋና ገንዘብ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 163/71 መሠረት የዘቀጠ ትርፍ በየበጀት ዓመቱ መሰብሰብ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡፡ በዚሁ መሠረት በበጀት ዓመቱ ከዘቀጠ ትርፍ ብር 33,992,394.00 እንደዚሁም ከትርፍ ድርሻ ክፍያ ብር 535,864,092.00 የተሰበሰበ መሆኑ በቀረበው ገቢና ወጪ መግለጫ ላይ ለማወቅ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ ከአዋጅ ቁጥር 25/1984 በፊት የነበረው ውዝፍ የዋና ገንዘብና የዘቀጠ ትርፍ እንዲሁም በአዋጅ ቁጥር 163/71 የሚተዳደሩት ድርጅቶች የሚፈለግባቸውን የዘቀጠ ትርፍና ከአዋጅ ቁጥር 121/87 በፊት የሚፈለግባቸውን የዋና ገንዘብ መሰብሰቡን ለማጣራት ተሞክሮ በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት ኦዲቱን ማከናወን ሳይቻል ቀርቷል፡፡

- በየድርጅቶቹ ስም የተከፈተው ሌጀር በአብዛኛው በእርሳስ የተመዘገበና ከፊሉ በኮምፒዩተር ላይ የተመዘገበ ቢሆንም የተወሰኑት ደግሞ ያልተመዘገቡ በመሆኑ፣
- በናሙና ከተመረጡት ድርጅቶች ውስጥ በድርጅቶቹ የኦዲት ሪፖርት ላይ የተመለከተው ተከፋይ ሂሣብ እና በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በተዘጋጀው ሌጀር መሠረት ከድርጅቶቹ የሚፈለገው ሂሳብ የተለያየ ሆኖ መገኘቱ/ እንደዚሁም በሌጀር ላይ የተመለከተውን በኦዲት ሪፖርት ላይ ለማግኘት አለመቻሉ፣
- በሌጀር ላይ ተሰብስቧል ተብሎ ለተያዘው ሂሣብ ገቢ መሆኑን የሚያረጋግጥ የባንክ ክሬዲት አድቫይስ ሊቀርብ አለመቻሉ፣
- ለኦዲት የሚፈለጉትን የድርጅቶች ፋይል በቀላሉና በአጭር ጊዜ ለማግኘት አለመቻሉ፣

ከላይ በተመለከቱት ሁኔታዎች ምክንያት ኦዲቱን ማከናወን ያልተቻለ ሲሆን፣ ይህ ጉዳይ በየዓመቱ በኦዲት ሪፖርት የሚነሳ ችግር በመሆኑ አሠራሩን ለማሻሻልና የድርጅቶችን ዕዳ ለመወሰን ከድርጅቶቹ የተመረመረውን የሂሳብ ሪፖርት መነሻ በማድረግ ያለባቸውን የዘቀጠ ትርፍና የመንግሥት ዋና ገንዘብ በአዲስ ሌጀሮች ላይ የመመዝገብ ሥራ መጀመሩን፣ ከዚህም በተጨማሪ ውዝፍ

የዘቀጠ ትርፍና የመንግሥት ዋና ክፍያ መክፈል የማይችሉ ድርጅቶች ተለይተው ተሰብሳቢ ሂሳብ የሚሰረዝበት ሁኔታ በማመቻቸት ላይ መሆኑን ገልጸዋል::

በመሆኑም ለወደፊቱ በተገለፀው መልኩ ሂሳቡ ተስተካክሎ ኦዲት የሚደረግበት ሁኔታ በአፋጣኝ እንዲመቻች እናሳስባለን::

3. <u>የመልሶ ማበደር ሂሳብ</u>

መንግሥት ከውጭ አገር ተበድሮ በመልሶ ማበደር ስምምነቶች ለልማት ድርጅቶች ያበደረውን ገንዘብ ተበዳሪዎች በገቡት ውል መሠረት ወቅቱን ጠብቀው ተመላሽ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በበጀት ዓመቱ የተሰበሰበው ዋና ገንዘብ ብር 132,428,133 እንደዚሁም የወለድ ክፍያ ብር 143,157,794 ገቢ የተደረገ ለመሆኑ በዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ ላይ ተመልክቷል::

የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ፣ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን፣ የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ለኦዲት በናሙና ተመርጠው ዕዳቸውን በገቡት ውል መሠረት መክፈላቸውን ለማጣራት በተሞከረበት ወቅት የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና ኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ የተበደሩትን የገንዘብ መጠን፣ ተመላሽ ያደረጉትንና ያለባቸውን ቀሪ እዳ የሚያሳይ የሂሳብ መዝገብ ባለመቅረቡ ኦዲቱን ለማከናወን ያልተቻለ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን (8 ብድሮች)፣ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን (12 ብድሮች) እና በፊንጫ ስኳር ፋብሪካ (3 ብድሮች) ላይ ዝርዝር ኦዲት ተደርጓል::

በተደረገው ኦዲት የሚከተሉት ሁኔታዎች ተገኝተዋል::

3.1 <u>በወቅቱ ተመላሽ ያልተደረገ ሂሳብ ብር 126.56 ሚሊዮን</u>

እስከ ሰኔ 30/1996 ዓ.ም ድረስ ከኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ተመላሽ መደረግ ሲገባው በብድር ስምምነቱ መሠረት ያልተሰበሰበ የዋና ገንዘብ ብር 52.57 ሚሊዮን፣ የብድር ወለድ ብር 73.99 ሚሊዮን በድምሩ ብር 126.56 ሚሊዮን ተገኝቷል:: ከተጠቀሰው ሂሳብ ውስጥ ተመላሽ ሳይደረግ ከ10 ዓመት በላይ የቆየ ሂሳብ የሚገኝበት ሲሆን በወቅቱ

ያልተሰበሰበውም ሂሳብ በዓመታዊ የገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫው ውስጥ አልተካተተም፡፡

በብድር ስምምነቱ መሠረት ተመላሽ ያልተደረገውን ሂሳብ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ለውጭ አበዳሪዎች ወቅቱን ጠብቆ ክፍያ የመፈጸም ግዴታ ያለበት ሲሆን ዕዳው የተከፈለላቸው ድርጅቶች ደግሞ በገቡት ውል መሠረት ያለባቸውን የመንግሥት ዕዳ መክፈል ይጠበቅባቸዋል፡፡ በመሆኑም ግዴታቸውን በማይወጡ ድርጅቶች ላይ ጠበቅ ያለ እርምጃ በመውሰድና ክትትል በማድረግ የመንግሥት ገንዘብ ወቅቱን ጠብቆ እንዲሰበሰብ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፡፡

### 3.2 ተመላሽ ለመደረጉ ማስረጃ /የባንክ ክሬዲት አድቫይስ/ ያልቀረበለት ሂሣብ ብር 134,790,976

በመልሶ ማበደር ሂሣብ ሌጀር ላይ የተመዘገበው ሂሳብ ትክክል መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ ለኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ከተሰጠው ብድር ውስጥ ተመላሽ የተደረገ ተብሎ የተመዘገበና ከእዳ ላይ የተቀናነሰ ብር 134,790,976.00 የተገኘ ሲሆን ሂሣቡ በትክክል ገቢ የተደረገ መሆኑን ለማረጋገጥ ተበዳሪው ገንዘቡን ገቢ ያደረገበት ማስረጃ /ባንክ ክሬዲት አድቫይስ/ ሊቀርብ ባለመቻሉ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡ ስለሁኔታው የብድር አስተዳደር መምሪያ ተጠይቆ ገቢዎቹ የረጅም ዓመታት በመሆናቸው ማስረጃዎችን በቅርብ ማግኘት እንደማይቻል ሆኖም ግን የተወሰኑትን ገቢዎች ከማዕከላዊ ሂሣብ መምሪያ ከተገኙ የገቢ ዝርዝር ማስረጃዎች ጋር በማመሳከር ሂሳቡ በትክክል ገቢ የተደረገ መሆኑ እንደተረጋገጠ ገልፀዋል፡፡ ይሁን እንጂ ዋናው ማስረጃ ባንክ ገቢ የተደረገበት አድቫይስ ሊሆን ስለሚገባ አስፈላጊው ጥረት ተደርጎ ማስረጃዎች ሊሟሉ የሚችሉበት መንገድ ሊፈለግ ይገባል፡፡

### 3.3 የብድር ማስታወቂያ /Loan disbursement voucher/ ያልቀረበለት ሂሳብ ብር 25,933,980.02

የመልሶ ማበደር ሂሳብ ኦዲት በተደረገበት ወቅት ከተለያዩ የውጭ አገር አበዳሪዎች ለቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ያስተላለፉትን የገንዘብ መጠን የሚገልጽ የብድር ገንዘብ ማስተላለፊያ ማስታወቂያ (suppliers invoice)

ያልቀረበለት ብር 25,933,980.00 በገቢ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡ አበዳሪዎች ለሚኒስቴር መ/ቤቱ የላኩት የብድር ማስታወቂያዎች ለኦዲት ባለመቅረባቸው በገቢ የተያዘውን ሂሳብ ትክክለኛነት ለማጣራት ሳይቻል ቀርቷል፡፡ በመሆኑም ለኦዲት ያልቀረቡት የብድር ማስታወቂያዎች (Supplier invoice) ተሟልተው መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ ባጠቃላይ ስላልቀረቡት ማስረጃዎች ጉዳይ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ለማሟላት ጥረት የሚደረግ መሆኑን ኦዲት አስደራጊዎች ገልጸዋል፡፡

## 4. <u>የአገር ውስጥ ብድር ገቢ</u>

መንግሥት የሚያጋጥመውን የበጀት እጥረት ለመሸፈን አገር ውስጥ ከሚገኙ የፋይናንስ ተቋማት የተበደረው ሂሳብ በትክክል በገቢና በወጪ መመዝገቡን እንደዚሁም በዓመታዊ ሂሳብ መግለጫ መካተቱን ለማረጋገጥ በተደረገው ኦዲት

### 4.1 <u>ብሔራዊ ባንክ በሚልከው የሂሣብ ማስታወቂያና በብድር አስተዳደር መምሪያ የሂሳብ ሌጀር መካከል የታየ ልዩነት</u>

የአገር ውስጥ ብድርን ሂሳብ ለመከታተል በብድር አስተዳደር መምሪያ የተያዘው መዝገብና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የአገር ውስጥ ብድርን ሂሳብ በተመለከተ በየወሩ ከሚልከው የሂሳብ ማስታወቂያዎች ጋር ሲገናዘብ ሰኔ 30/1996 ብሔራዊ ባንክ የላከው የግምጃ ቤት ሰነድ ቀሪ ዕዳ ማስታወቂያ በብድር አስተዳደር መምሪያ መዝገብ ላይ ከተመለከተው በብር 3,06.9 ሚሊዮን እንዲሁም በተመሳሳይ ሁኔታ የቦንድ ቀሪ ዕዳ በብር 238.5 ሚሊዮን አንሶ ተገኝቷል፡፡

የልዩነቱ መንስኤ አንዳንድ የብድር ሂሳቦች ክፍያ በብሔራዊ ባንክ በኩል በወቅቱ ባለመመዝገባቸው እና የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር እና የብሔራዊ ባንክ የሂሳብ መዝጊያ ወቅት በመለያየቱ ሲሆን፣ የቦንድ እና ሌሎች እንደ ትሬዠሪ ቢልና የቀጥታ ብድር ሂሳብ አመዛጋገብ ከባንኩ ጋር በመነጋገር መፍትሔ እንደሚሰጥበትና እስከዚያው ድረስ ግን ባንኩ በየወሩ በሚልከው ሪፖርትና በመምሪያው የሂሳብ መዝገብ መካከል የሚታዩ ልዩነቶችን በየወሩ በቋሚነት የማስታረቅ ሥራ እንደሚሰሩ ገልጸዋል፡፡

ስለሆነም መምሪያው የሚያዘጋጀው የብድር መከታተያ መዝገብ ከብሔራዊ ባንክ በየወሩ ከሚላከው ሪፖርት ጋር በማገናዘብ ልዩነት ሲከሰት ወቅታዊ የሆነ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል፡፡

## 4.2 ከመበደሪያ ጣሪያ በላይ የተፈፀመ የአገር ውስጥ ብድር

በገንዘብና የባንክ አዋጅ ቁጥር 83/86 አንቀጽ 25 (3) መሠረት በአንድ በጀት ዓመት ውስጥ መንግሥት ሊሸጥ የሚችለው የግምጃ ቤት ሰነድ ባለፉት ሦስት ተከታታይ በጀት ዓመታት ውስጥ ከተሰበሰበው አማካይ የመንግሥት መደበኛ ገቢ 25% መብለጥ እንደሌለበት የተደነገገ ሲሆን በ1993፣ በ1994፣ እና በ1995 በጀት ዓመታት የተሰበሰበ አማካኝ መደበኛ ገቢ ብር 8,627.7 ሚሊዮን ነው፡፡ የዚህም 25% ብር 2,157 ሚሊዮን ሲሆን፣ በ1996 በጀት ዓመት መንግሥት በግምጃ ቤት ሰነድ አማካኝነት የተበደረው ብር 3,402.4 ሚሊዮን መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ብር 1,245.4 በአዋጅ ከተፈቀደው በላይ ብድር የተፈጸመ መሆኑ ታውቋል፡፡

በመሆኑም ለወደፊቱ በወጣው አዋጅ መሠረት ብድሩ መከናወን ያለበት ስለሆነ ከተገቢው የመበደሪያ ጣሪያ በላይ ብድር እንዳይፈጸም ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

## 4.3 የውጭ አገር ዕርዳታ ሂሳብ ሪፖርት አቀራረብ ለክትትል የማያመች ስለመሆኑ

በበጀት ዓመቱ መንግሥት በዕርዳታ ያገኘው ገቢ በሙሉ በዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ የተካተተ መሆኑን ለማጣራት ተሞክሮ በቻናል 2 (Channel 2) ዕርዳታ ያገኙ ድርጅቶች ካቀረቡት ወርኃዊ ሪፖርት በስተቀር ወደ አገር ውስጥ የገባውን የዕርዳታ መጠን የሚገልፅ ማስረጃ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በኩል ሊቀርብ አልቻለም፡፡

በበጀት ዓመቱ ያገኙትን የዕርዳታ መጠን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ በወርኃዊ ሪፖርት አማካኝነት ያላሳወቁ መ/ቤቶች ቢኖሩ የነዚህ መ/ቤቶች ሂሳብ መግለጫው ውስጥ ሳይካተት የሚቀር በመሆኑ የበጀት ዓመቱ የዕርዳታ ገቢ በሂሳብ መግለጫው ላይ የተመለከተው ብቻ ይሆናል ለማለት አዳጋች ነው፡፡

ሚኒስቴር መ/ቤቱ ይህንን ሂሳብ ለመከታተል ባለበጀት መ/ቤቶች ያገኙትን ዕርዳታ እንዲያሳውቁ በደብዳቤ የሚጠይቅ መሆኑን፣ የተለየ የባንክ ሂሳብ በባለበጀት መ/ቤቶች እንዲከፈት ማድረጉን እና ያገኙትን እርዳታ ሥራ ላይ አውለው ሪፖርት ሲያቀርቡ በተጨማሪ በጀትነት እየተመዘገበ እንደሆነ ቢታወቅም፤ ዕርዳታ አግኝተው ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ሪፖርት ያላደረጉ መ/ቤቶች ቢኖሩ ሊታወቅ የሚችልበት የአሰራር ስርዓት አለመኖሩ ታውቋል፡፡

የሚኒስቴር መ/ቤቱ የመልቲላተራል እና የመንግሥታት ትብብር መምሪያዎች ከዕርዳታ ሰጪዎች ጋር የቀረበ ግንኙነት ያላቸው በመሆኑ ወደ አገር ውስጥ የገባውን የገንዘብ እና የዓይነት እርዳታ መጠን ለማወቅ የሚያስችል መረጃ የሚይዙ ሲሆን፣ የማዕከላዊ ሂሳብ መምሪያ ይህንኑ መሠረት በማድረግ ዕርዳታ ደርሷቸው ሪፖርት ያላቀረቡ መ/ቤቶችን በመከታተል ትክክለኛውን የዕርዳታ ብድር መጠን መመዝገብና በዓመታዊ ሂሳብ መግለጫ ላይ ማካተት ይኖርበታል፡፡

## 5. የወጪ ሂሳብ፣

በዓመታዊ የገቢና የወጪ ሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የወጪ ሂሳብ ትክክለኛነት ለማጣራት በተደረገው ኦዲት ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል፡፡

### 5.1 በቀጥታ ወጪ ተይዞ ስለተገኘው ለክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች የተሰጠ ሂሳብ ብር 5,312.9 ሚሊዮን

በዓመታዊ ገቢና ወጪ ሂሳብ መግለጫ ላይ የተመለከተው የድጎማ ወጪ ሂሳብ ሥራ ላይ የዋለበት ሁኔታ የሚገልጽ የሂሳብ ማስታወቂያ የቀረበለት መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፣ በበጀት ዓመቱ ለክልሎችና ለከተማ መስተዳድሮች የተከፈለ ብር 5,312.9 ሚሊዮን ሥራ ላይ የዋለበት ሁኔታ ሳይረጋገጥና ሪፖርት ሳይቀርብለት በቀጥታ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፋይናንስ አስተዳደር ደንብ ቁጥር 17/1989 አንቀጽ 79 እና አንቀጽ 74 (4) የመንግሥት ሂሳብ ሪፖርት በፌዴራልና በክልል መንግሥታት መካከል የተደረጉትን የፋይናንስ እንቅስቃሴዎች፣ የክልል መንግሥታትን የድጋፍ በጀት አፈፃፀም ከፋይናንስ ዕቅዱ ጋር በማነፃፀር

የፌዴራልና የክልል መንግሥታትን የፋይናንስ ሁኔታ የሚያሳይ የበጀት ዓመቱን የመጨረሻ ሪፖርት በተጠቃለለና በተነፃፀረ መልኩ የሚይዝ እንደሚሆን እና የክልል መንግሥታትም ከፌዴራል መንግሥት የተሰጣቸውን የበጀት ድጋፍና የውስጥ ገቢያቸውን በየወሩና በየሩብ ዓመቱ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ማቅረብ እንዳለባቸው በግልጽ ተደንግጓል።

ከዚህ በተጨማሪም የድጎማ ሂሳብ ሥራ ላይ የዋለበት ሁኔታ ሳይታወቅ የተዘጋጀው የመንግሥት ዓመታዊ የገቢና የወጪ ሂሳብ መግለጫ አቀራረብ ለፖሊሲ አውጪው አካል አሳሳችና የአገሪቱን ትክክለኛ ዓመታዊ ገቢና ወጪ አጠቃሎ የማያሳይ በመሆኑ መታረም እንዳለበት ባለፉት ዓመታት የኦዲት ሪፖርት አስተያየት የተሰጠበት መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ ለጉዳዩ የመጨረሻ እልባት ለመስጠት በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ከፍተኛ ኃላፊዎች ደረጃ ውይይት ተደርጓል። በዚህ መሠረት ለክልሎች የተላለፈው በጀት ሥራ ላይ እንደዋለ ተቆጥሮ በወጪ መመዝገብ እንደሌለበት እና በሂሣብ መግለጫው ውስጥ መካተት ያለበት ሂሳብ ሥራ ላይ የዋለው ትክክለኛው ወጪ መሆን እንደሚገባው በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር እና በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ከፍተኛ ኃላፊዎች ደረጃ ስምምነት የተደረሰ ሲሆን፣ ከሂሳብ አያያዝ እና ከኦዲት አንፃር በማየት ሂሳቡ በወጪ የሚመዘገብበትን ሁኔታ የሚያጠና ከሁለቱ መ/ቤቶች የተውጣጡ አባላት ያሉበት የቴክኒክ ኮሚቴ ተቋቁሟል። ስለሆነም የቴክኒክ ኮሚቴው በአፋጣኝ አስፈላጊውን የውሳኔ ኃሳብ እንዲያቀርብ ክትትል ተደርጎ ጉዳዩ የመጨረሻ እልባት እንዲሰጠው እናሳስባለን።

## 6. <u>የበጀት ሂሳብ</u>

### 6.1 <u>በ1996 በጀት ዓመት የበጀት አፈፃፀምና ሥራ ላይ የዋለ በጀት ሂሣብ ኦዲት</u>

በበጀት ዓመቱ በሥራ ላይ ይውላል ተብሎ ከተመለከተው ጠቅላላ የተስተካከለ በጀት ብር 22,968.5 ሚሊዮን ውስጥ የገንዘብ ሚኒስቴር ባቀረበው የሂሳብ መግለጫ መሠረት በሥራ ላይ የዋለው ብር 19,978.2 ሚሊዮን ወይም የበጀቱ 86.98% ሲሆን ከዚህ ውስጥ ለመደበኛ በጀት ወጪ የተደረገው ብር 8,410.2

ሚሊዮን በተስተካከለ በጀት ከተያዘው ብር 8,842.4 ሚሊዮን ሲነፃፀር ብር 432.2 ሚሊዮን ወይም 4.89% በማነስ አሳይቷል:: ለካፒታል በጀት ወጪ የተደረገው ብር 6255.1 ሚለዮን ከተስተካከለው በጀት ብር 8,095.8 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር በብር 1,840.7 ሚሊዮን ወይም በ22.74% ያነሰ ሲሆን ለክልሎች የተሰጠው ጠቅላላ ድጋፍ ብር 5,312.9 ሚሊዮን ከተስተካከለው በጀት ብር 6,030.3 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር በብር 717.4 ሚሊዮን ወይም 11.9% አንሶ ተገኝቷል::

የበጀት ዘመኑ ጠቅላላ ወጪ ብር 19,978.2 ሚሊዮን ከ1995 በጀት ብር 16,382.9 ሚሊዮን ጋር ሲነፃፀር ደግሞ ብር 3,595.3 ሚሊዮን ወይም 18% ብልጫ አለው::

ዝርዝሩም ቀጥሎ ቀርቧል::

| የበጀቱ ዓይነት | የ1996 በጀት ዓመት | | | ልዩነት ከተስተካከለ በጀት (በመብለጥ) በማነስ | የ1995 በጀት ዓመት ወጪ | የ1995 ከ1996 ወጪ ልዩነት በመብለጥ (በማነስ) |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የታወጀ በጀት | የተስተካከ ለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለ ወጪ | | | |
| መደበኛ | 7885.5 | 8842.4 | 8410.2 | 432.2 | 6903.2 | 1507.0 |
| ካፒታል | 5429.4 | 8095.8 | 6255.1 | 1840.7 | 4582.3 | 1672.8 |
| የክልሎች ድጋፍ | 5969.8 | 6030.3 | 5312.9 | 717.4 | 4897.4 | 415.5 |
| | | | | | | |
| | 19284.7 | 22968.5 | 19978.2 | 2990.3 | 16382.9 | 3595.3 |

## 6.2 <u>ከበጀት በላይ ሥራ ላይ ስለዋለው ብር 372.93 ሚሊዮን ሂሳብ</u>

በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 57/89 አንቀጽ 18/1 መሠረት በመንግሥት መ/ቤቶች ውስጥ የሚደረግ የበጀት ዝውውር መደበኛ በጀትን በሚመለከት በዋና ሂሣብ መደቦች ውስጥ የሚደረግ የበጀት ዝውውር ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር እየቀረበ ተፈፃሚ መሆን እንደሚገባው ይደነግጋል::

ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ የኦዲት ዘዴን በመከተል በተደረገው ኦዲት በበርካታ መ/ቤቶች የበጀት ዝውውር ሳይደረግ ከተደለደለው በጀት በላይ

ወጪ የሆነ ብር 147.61 ሚሊዮን (አባሪ 2)፣ የተደለደለ በጀት ሳይኖር ሥራ ላይ የዋለ ብር 15.95 ሚሊዮን (አባሪ 1) በድምሩ ብር 163.56 ከበጀት በላይ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል።

ከበጀት በላይ ወጪ ስለተደረገው ሂሳብ የበጀት ዓመቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ባለበጀት መ/ቤቶች ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በላኩት ዘገባ ላይ የተለያዩ ምክንያቶች የሰጡ ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ ያለፉት ዓመታት የሰነድ ሂሳብ በቀጣዩ በጀት ዓመት በወጪ በመመዝገቡ፣ ከውስጥ ገቢ ተጠቅመው በመገኘታቸው፣ ለተጨማሪ እሴት ታክስ በቂ በጀት ሳይያዝ በመቅረቱ፣ በተለይ ከፍተኛ ድርሻውን የያዘው የትምህርት ሚኒስቴር ግንቦት 1996 ዓ/ም የተጀመረው የዜሮ ሚዛን አሠራር የበጀት ምዝገባ መዛባት ያስከተለበት መሆኑን ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ለወደፊቱም መ/ቤቶች የፋይናንስ አዋጅና ደንብ ጠብቀው እንዲሰሩ የሚያስችል የበጀት ዝውውር መመሪያ መዘጋጀቱ ተገልጿል።

ስለሆነም ባለፉት ሪፖርቶቻችን እነደገለጽነው የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ከተሰጠው የመንግስትን ሀብት በበላይነት የማስተዳደር ኃላፊነት አንፃር የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅና ደንብን በመተላለፍ ከተፈቀደላቸው በጀት በላይ በሚጠቀሙ መ/ቤቶች ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል የሚደረግበትን እና አዋጅና ደንቡን ተከትለው በማይሰሩት ላይ ደግሞ የሚጠየቁበትን አሠራር መዘርጋት ያለበት ሲሆን ሁኔታውን ለማስተካከል በሚረዳ መልኩ እየተዘጋጀ ያለው የበጀት ዝውውር መመሪያ ባስቸኳይ ተግባር ላይ እንዲውል ተገቢው ክትትል መደረግ ይኖርበታል።

## 6.3 <u>ስላልተሠራበት በጀት ሂሳብ</u>

## <u>ብር 2,981.05 ሚሊዮን</u>

በልዩ ልዩ የወጪ ሂሳብ መደብ ለበርካታ መ/ቤቶች ከተደለደለው በጀት ውስጥ በእያንዳንዱ የወጪ ሂሳብ መደብ ከብር 1 ሚሊዮን በላይ ሥራ ላይ ያልዋለው የበጀት መጠን ብቻ ብር 2,757.15 መሆኑ ተረጋግጧል።

ሥራ ላይ ካልዋለው በጀት ውስጥ ብር 551.4 ሚሊዮን መ/ቤቶች የተስተካከለ በጀት ኖሯቸው ሙሉ በሙሉ ሥራ ላይ ሳያውሉት የተገኘ በጀት ነው። (አባሪ 3)

ስለዚህ ለወደፊቱ የመንግሥት በጀት አጠቃቀም በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና የበጀት ዓዋጅ መሠረት ተገቢው ክትትል እየተደረገ ለዘመኑ የተመደበው በጀት ሥራ ላይ የሚውልበት መንገድ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡

የማይሰሩበትን በጀት በማስፈቀድ ሌሎች መ/ቤቶች ሊሰሩ የሚችሉበትን በጀት ያለአግባብ በሚይዙ መ/ቤቶች የበጀት አፈቃቀድ ወቅት የመ/ቤቶቹ የአለፉት አመታት የበጀት አፈፃፀም ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡

## 7. ልዩ ልዩ

- በብልጫ ተመዝግቦ የተገኘ የመልሶ ማበደር ወለድ ሂሣብ ብር 407,438.32 መገኘቱ፣
- በአገር ውስጥ የብድር ወለድና የባንክ አገልግሎት ክፍያ የሂሳብ መደብ 6434 መመዝገብ የሚገባው ብር 514,000.00 በ28 ቀን የግምጃ ቤት ሰነድ በተከፋይ የሂሳብ መደብ 5042 ብር 506,000 እና በ91 ቀን የግምጃ ቤት ሰነድ በተከፋይ የሂሳብ መደብ 5043 ብር 8,000 ተመዝግቦ መገኘቱ፣

ታውቋል፡፡

ከላይ የተመለከቱት የአሰራር ግድፈቶች ሊታረሙና ሊስተካከሉ ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት ለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡